ቀን 23 ነሐሴ 2011
Date

ቁጥር 27/18/1638
Ref. No.


የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Trade and Industry


- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
  ለንግድ ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ
  <u>ባሕር ዳር</u>
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
  ለንግድ ቢሮ
  <u>አዲስ አበባ</u>
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
  ንግድ ቢሮ
  <u>አዲስ አበባ</u>
- በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
  ለንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ
  <u>መቀሌ</u>
- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
  ለንግድና ገበያ ልማት ቢሮ
  <u>ሃዋሳ</u>
- በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
  ለንግድና ትራንስፖርት ቢሮ
  <u>ጅጅጋ</u>
- በድሬዳዋ አስተዳደር
  ለንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ
  <u>ድሬዳዋ</u>
- በሐረሪ ክልላዊ መንግሥት
  ለንግድ ኢንዱስትሪና፣ ከተማ ልማት ቢሮ/
  <u>ሐረሪ</u>
- በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
  ለንግድ፣ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ
  <u>ሠመራ</u>
- በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
  ለንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ
  <u>አሶሳ</u>
- በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
  ለንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ
  <u>ጋምቤላ</u>

ጉዳዩ፦ <u>የምግብ ዘይት አቅርቦትና ስርጭት ማስፈፀሚያ መመሪያ መላኩን ይመለከታል</u>

የምግብ ዘይት አቅርቦት ስርጭት ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 020/2011 ተግባራዊ እንዲሆን ከዚህ ደብዳቤ ጋር 19 ገፅ አባሪ አድርገን የላክን ሲሆን በመመሪያው መሰረት የምግብ ዘይት አቅራቢዎችን እስከ ጳጉሜ 6/2011 ዓ.ም ድረስ እጅግ በጣም ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ መልምላችሁ እንድታሳውቁን በጥብቅ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

Ministry Of Trade & Industry
Archives
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት

<u>እንዲያውቁት</u>
- ለክቡር የንግድ አሰራርና ሬጉላቶሪ ዘርፍ ሚ/ድኤታ
  <u>ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>

<u>ግልባጭ</u>
- ለገበያ ድርጅት ኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ዳሬክቶሬት/ያለ አባሪ/
  <u>ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>


☎ +251-551 8025/29
+251-557 5866
✉ 704
Fax: +251-551 5411, 552 3416
+251-553 1027, 554 0286
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

# የምግብ ዘይት አቅርቦት እና ስርጭት ማስፈጸሚያ

# መመሪያ ቁጥር 557/2013

ነሀሴ 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

# የምግብ ዘይት አቅርቦት እና ስርጭት ማስፈጸሚያ መመሪያ 557/2013

በመሰረታዊ ሸቀጥነት ከተለዩ ምርቶች ውስጥ የምግብ ዘይት አንዱ በመሆኑ ከህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ጋር ተገናዝቦ ፣ የተጣራ ምግብ ዘይት አቅርቦት፣ ስርጭት እና ዋጋ ቁጥጥር እየተደረገበት ለህብረተሰቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አስመጪዎችን መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ሃገሪቱ ከዉጭ ሃገር በመንግስት ድጎማ ፃምታስመጣዉ የምግብ ዘይት በሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች በማምረት ቀስ በቀስ የምግብ ዘይት ፍላጎት ማሟላት እና ከአቅርቦት እስከ ስርጭት ያለውን የንግድ ሰንሰለት ቁጥጥርና ድጋፍ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዘርፉ ተሳታፊ የሚሆኑትን ተዋናዮች የመምረጥ ሂደት ላይ ግልጽነት እንዲኖረው ማድረግ፣ እንዲሁም ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና በተዋረድ የሚገኙ የአስተዳደር አካላት ተሳትፎ አስፈላጊነት የታመነበት በመሆኑ፤

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢፌዲሪ አስፈጻሚ አካላት ተግባርና ሥልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 ዓ.ም አንቀጽ 19(1-በ) መሰረት ለማስፈጸም ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "የምግብ ዘይት አቅርቦት እና ስርጭት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 557/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. የቃላት ትርጓሜ

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

1) " የምግብ ዘይት" ማለት ከአትክልት እና ከቅባት እህሎች ምርት፣ የተመረተ እና ሙሉ በሙሉ የማምረት ሂደቱን ጨርሶ በቀጥታ ለምግብነት አገልግሎት የተዘጋጀ እና የሀገሪቱን አስገዳጅ የምግብ ዘይት ደረጃ መስፈርት የሚያሟላ ነው፡፡

2) "መስፈርት" ማለት የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶችን ለመመልመል እና ለመምረጥ የሚጠየቁ እና መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፤

3) "አስመጪ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት በመንግስት የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ማናቸውንም የምግብ ዘይት ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስመጣ ሰው ነው፤

4) "መረጣ" ማለት መስፈርቱን የሚያሟሉትን በመለየት የምግብ ዘይት አስመጪ እንዲሆኑ ጉዳዩ በሚመለታቸው በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል የሚመረጡ ናቸው፤

5) "ሚኒስቴር" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማለት ነው፤

6) "ክልል" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትንና ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደርንም ይጨምራል፤

7) "ቢሮ" ማለት በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሠጣቸው አካላት ናቸው፤

8) "ቸርቻሮ ሻጭ" ማለት የምግብ ዘይት ለመጨረሻው ተጠቃሚ የሚያቀርቡ በዚህ መመሪያ መሠረት ትስስር ውስጥ የገቡ ነጋዴዎች፣ ህብረት ስራ ማህበራት እና ሸማች ህብረት ስራ ማህበራት ናቸው፤

9) "የመጨረሻ ተጠቃሚ" ማለት ከባለ ኮከብ ሆቴሎች፣ሪዞርቶች እና ፋብሪካዎች በስተቀር በዚህ መመሪያ መሰረት ቁጥጥር የሚደረግባቸው የምግብ ዘይቶችን አገልግሎት ለመስጠት፣ ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ ፍጆታ የሚገዛ ማንኛውም ሰው ነው፤

10) "የህብረት ስራ ማህበራት" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የምግብ ዘይቶች በማሰራጨት ሂደት ተሳታፊ የሆኑትን ብቻ ይይዛል፤

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

11) "የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚችሉትን የምግብ ዘይቶች በማሰራጨት ሂደት ተሳታፊ የሆኑትን ብቻ ይይዛል፣

12) "አስተዳደራዊ እርምጃ" ማለት ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት ሲባል የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መሥጠት፣ ማገድ፣ ማሸግ፣ መሰረዝና የመሳሰሉት በአስፈጻሚ አካላት የሚወሰዱ እርመጃዎች ናቸው፤

13) "አገልግሎት ሰጪ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የምግብ ዘይቶች በግብአትነት ተጠቅሞ እሴት በመጨመር በቀጥታ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋም ሆኖ ማናቸውንም ፋብሪካዎች፣ ሪዞርቶች እና ባለ ኮከብ ሆቴሎችን አያካትትም፤

14) "የመንግስት ተቋማት" በዚህ መመሪያ መሰረት ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የምግብ ዘይቶች ኮታ የሚመደብላቸው እንደ ከፍተኛ የትምርት ተቋማት፣ የመከላከያ ሰራዊት፣ የፌደራል ማረሚያ ቤቶች፣ የፌደራል ፖሊስ እና መሰል ሌሎች ተቋማት ሆነው የምግብ ዘይትን ለማግኘት ከመንግስት የይሁንታ ፈቃድ የሚሰጣቸውን ያካትታል፤

15) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው፤

3. የተፈጻሚነት ወሰን

በዚህ መመሪያ መሰረት የምግብ ዘይትን የሚያስመጣ ወይም የሚያሰራጭ ማንኛውንም ሰው ነው::

4. የምግብ ዘይት አስመጪዎች ብዛት፤

1) አስመጪዎች በሚያስመጡት ምርት በአዋጭ ንግድ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆን እና ውድድሩ ፍትሃዊ እንዲሆን የአስመጪዎች ቁጥር 20 ብቻ ይሆናል፤

2) በእያንዳንዱ ክልል የሚመርጠው የአስመጪዎች ብዛት ለክልሉ በተመደበው ኮታ መሠረት በማድረግ ሆኖ ክልሉ፡-

ሀ/ በወር 2 ሚሊዮን ሊትር እና ከዚያ በታች የሚጠቀም ከሆነ 1 አስመጪ፤

ለ/ በወር ከ2 — 5 ሚሊዮን ሊትር የሚጠቀም ከሆነ 2 አስመጪ፤

ሐ/ በወር ከ 5 በላይ — 10 ሚሊዮን ሊትር የሚጠቀም ከሆነ 3 አስመጪ እና

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

መ/ በወር ከ10 ሚሊዮን በላይ ሊትር የሚጠቀም ከሆነ 5 አስመጪ የሚመርጥ ይሆናል፡፡

3. ከአንድ በላይ አስመጪዎች በሚመረጡበት ጊዜ የሚያስመጡት የምግብ ዘይት መጠን ድልድል እኩል ወይም የተመጣጠነ እንዲሆን ይደረጋል፤

## 5. የማወዳደሪያ መስፈርቶች

1. ካፒታል-48%
2. የአስመጪነት የስራ ልምድ-47%
3. የተመሰከረለት የኢኮኖሚ አንቅሳቃሽ-5%

## 6. የምግብ ዘይት አስመጪዎች ማሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች

1) ከዚህ በፊት በማንኛውም የንግድ ዕቃ አስመጪነት የስራ ልምድ ያለው መሆን ይገባዋል፤

2) ምርቱን ከመነሻ ወደብ ወደ መሀል ሀገር ለማጓጓዝ አስመጪው የተመደበለትን ኮታ በአንድ ጊዜ ለማንሳት የከባድ ጭነት ተሽከርካሪ፣ መጋዘን እና ሌሎች አስፈላጊ የሎጂስቲክ አቅም በራሱ ወይም የኪራይ ውል በተሟላ ሁኔታ ማቅረብ የሚችል መሆን ይገባዋል፤

3) ስራውን ለመጀመር የሚያስችል ዝቅተኛው 100 ሚሊዮን ብር እና ከዛ በላይ የሚሆን መነሻ በጥሬ ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ መሆኑን በባንክ የተረጋገጠ እና ግብር የተከፈለበት ሰነድ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፤

4) ከዚህ በፊት አስመጪ የነበሩ አፈጻጸማቸው ችግር ያለባቸው መሆኑ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ከተረጋገጠ ሊወዳደሩ አይችሉም፤

5) የተጣራ ምግብ ዘይት አስመጪ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ከአንድ ክልል በላይ መወዳደርም ይሁን መመረጥ አይችልም፤

6) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1-5 የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው መንግስት በፖሊሲ ለውጥም ይሁን ወይም በማናቸውም ምክንያትና ጊዜ በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን የምግብ ዘይቶችን መጠንን መቀነስ ወይም ማስመጣትን ሊያስቆም ይችላል፤

## 7. ለመመልመያና መምረጫ መስፈርቶች ከ100 የተሰጡ ነጥቦች፣

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ውስጥ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ካፒታል መጠን አጠቃላይ 48% የተሰጠው ሲሆን ፡-

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

1.1. 150 ሚሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ በጥሬ ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ መሆኑን በባንክ የተረጋገጠ እና ግብር የተከፈለበት ሰነድ ማቅረብ የሚችል ሙሉውን (48%) የሚያገኝ ይሆናል፤

1.2. ከ130 እስከ 150 ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ መሆኑን በባንክ የተረጋገጠ እና ግብር የተከፈለበት ሰነድ ማቅረብ የሚችል ከጠቅላላ ከተቀመጠው (48%) ላይ (42%) የሚያገኝ ይሆናል፤

1.3. 115 እስከ 130 ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ መሆኑን በባንክ የተረጋገጠ እና ግብር የተከፈለበት ሰነድ ማቅረብ የሚችል ከጠቅላላ ከተቀመጠው (48%) ላይ (36%) የሚያገኝ ይሆናል፤

1.4. 100 እስከ 115 ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ መሆኑን በባንክ የተረጋገጠ እና ግብር የተከፈለበት ሰነድ ማቅረብ የሚችል ከጠቅላላ ከተቀመጠው (48%) ላይ (30%) የሚያገኝ ይሆናል፤

2. ከዚህ በፊት በማንኛውም የንግድ ዕቃ በድርጅቱ ስም የአስመጪነት ከ10 ዓመት በላይ የስራ ልምድ ያለው (47%) ፤

2.1. 10 ዓመት እና ከዚያ በላይ ልምድ ያለው ለዚህ ማወዳደሪያ ነጥብ የተሰጠውን ሙሉ (47%) የሚያገኝ ይሆናል፤

2.2. ከ7-9 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ለዚህ ማወዳደሪያ ነጥብ ከተሰጠው ሙሉ (47%) ውስጥ (41%) የሚያገኝ ይሆናል፤

2.3. ከ4-6 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ለዚህ ማወዳደሪያ ነጥብ ከተሰጠው ሙሉ (47%) ውስጥ (35%) የሚያገኝ ይሆናል፤

2.4. ከ3 ዓመት እና ከዚያ በታች የስራ ልምድ ያለው ለዚህ ማወዳደሪያ ነጥብ ከተሰጠው ሙሉ (47%) ውስጥ (29%) የሚያገኝ ይሆናል፤

<u>ማስታወሻ</u>፡ ተወዳዳሪዎች በእያንዳንዱ መወዳደሪያ ነጥብ ግማሽ/ከ0.5 እና ከዛ በላይ/ ካመጡ ከፍ ወዳለው እንዲሁም 0.5ን ሳይጨምር ከዛ በታች ነጥብ ካመጡ ዝቅ ወዳለው የተሰጠውን ነጥብ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

3. በጉምሩክ ኮሚሽን የተመሰከረላቸው ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች (Authorized Economic Operator) ሰርተፊኬት ላላቸው (5%) ፤

## 8. የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች መራጭ አካላቶች

የክልል ንግድ ቢሮ ሀላፊ ሰብሳቢ እና ስራውን የሚከታተለው ዳይሬክተር(የስራ ሂደት መሪ) ጸሀፊ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1) በክልል ኢንዱስትሪን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል፤



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

2) በክልል ጤናን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል፤

3) በክልል ህ/ስ/ማህበራትን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል፤

4) በክልል ኢንቨስትመንትን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል፤

5) በክልል ፍትህን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል፤

## 9. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

1) የምግብ ዘይትን የሚያስመጡ ሰዎችን መምረጫ መመሪያ እና መስፈርቶችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊም ያስደርጋል፤

2) የምግብ ዘይትን የሚያስመጡ አካላት ጊዜውን ጠብቀው ምርቱን ለህብረተሰቡ ማቅረብ የሚያስችላቸውን ቅድመ ሁኔታዎች (የውጭ ምንዛሪ እና ሌሎች መሰል) ተግባራትን በሚመለከታቸው የፌደራል ተቋማትን በማስተባበር እንዲመቻች ያደርጋል፤

3) በዚህ መመሪያ መሰረት ከውጭ ሀገር የሚገቡ የምግብ ዘይት ምርት አይነቶችን እና የጥራት ደረጃቸውን ይወስናል፤

4) የምግብ ዘይት አስመጪዎች መረጣ በዚህ መመሪያ መሰረት ስለመተግበሩ ያረጋግጣል፣ ቅሬታዎችን ያስተናግዳል የመጨረሻ ውሳኔም ይሰጣል፤

5) ይህ መመሪያ በስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ አፈጻጸሙን በየወሩ ከክልሎች ሪፖርት በመቀበል በመገምገም ለክልሎች ግብረ መልስ ስርአት በመዘርጋት አስፈላጊውን ተግባራት ያከናውናል፤

6) በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል የመረጣቸውን አስመጪዎች ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ መሰረት ሊያጸድቅ ወይም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሊሽር ይችላል፤

7) ፍላጎትን፣ አቅርቦትን፣ ስርጭትን እና ዋጋን በተመለከተ ጥናቶችን ያጠናል፣ ክትትል ያደርጋል፣ መረጃዎችን በማሰባሰብ አስፈላጊውን መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት እና ለተጠቃሚው እንዲደርስ ያደርጋል፤

8) ፍላጎት፤ አቅርቦት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የክልሎችን ኮታ ይወስናል፤

9) በልዩ ሁኔታ የሚስተናገዱ አካላት ማለትም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፤ የመከላከያ እና የፖሊስ ሰራዊት አካላት፣ ማረሚያ ቤቶች [illegible] ወይም ሰው



Ministry Of Trade & Industry Archives

ሰራሽ አገድጋዎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች እና የመሳሰሉትን ኮታ ይወስናል፤

10) የምግብ ዘይት አስመጪዎች መረጣ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰዎች በእኩልነት እንዲስተናገዱ መደረጉን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ማስተካከያዎች እንዲደረጉ ያደርጋል፤

11) የምግብ ዘይት መሰረታዊ ሸቀጥነትን ማብቂያ ጥናቶችን ያጠናል፤ ስልቶችንም ይነድፋል፤

12) አለም አቀፍ የምግብ ዘይት ዋጋን መሰረት በማድረግ በየ3 ወሩ የአስመጪዎችን እና የቸርቻሪዎችን መሸጫ ዋጋ ይወስናል፤

13) በመንግስት ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የምግብ ዘይቶች አቅርቦት፣ ክፍፍልና ስርጭት እንዲኖር ክልሎች ባሳተፈ ሁኔታ መረጃ ይሰበስባል፣ የማስፈፀሚያ እቅድ ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

14) የአስመጪዎችን እና የቸርቻሪዎችን የሥርጭት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ በተተመነው ዋጋ መሰረት መሸጡን ይከታተላል፤

15) የተጣራ የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች የሚያስመጡትን የምግብ ዘይት መጠን፣ በፓኬጅ ባለ (3 ሊ፣5ሊ፣10ሊ፣20ሊ፣25ሊ) ይወስናል እና የክልል የምግብ ዘይት ኮታ ይደለድላል፤

16) የምግብ ዘይቱን ከተቀመጠው የሥርጭት ሥርዓት ውጭ በሚያከማቹ፣ በሚያጓጉዙና በሚያሰራጩ አስመጪዎች ላይ የእርምት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

17) ስርጭቱንም በሚመለከት የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን በ3 ወሩ በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት ጋር ይገመግማል፤

18) በአቅርቦትና ስርጭቱ ዙሪያ ለሚከሰቱ ችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያመላክቱ የዳሰሳ ጥናት ያከናውናል፤

19) ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

10. በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት

1) በክልሉ የምግብ ዘይት አስመጪዎችን በዚህ መመሪያ መሰረት ይመርጣል፤

2) በክልል የተካሄደው የአስመጪዎች መረጣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጸደቀ በኋላ ከተመረጡት ጋር ውል ይፈራረማል፤

3) የምግብ ዘይት አስመጪዎችን መረጣ የሚያደርጉ አካላትን ያስተባብራል፤

4) የተመረጡ የምግብ ዘይት አስመጪዎች በውላቸው መሰረት ስለማስመጣታቸው እና ስለ ማድረሳቸው ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

5) በዚህ መመሪያ መሰረት ልዩ ሁኔታዎች ሲከሰቱ በወቅቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በማሳወቅ የኮታ ማሻሻያዎች እንዲደረግ ያደርጋል፤ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረትም ያስፈጽማል፤

6) በዚህ መመሪያ መሰረት የተመረጡ አስመጪዎች ለመመረጥ ያበቃቸው ጉዳዮች በወቅቱ ስለመፈጸማቸው የክትትል፣ ድጋፍ እና ቁጥጥር ተግባራትን በማከናወን ለሚንስቴር መ/ቤቱ ያሳውቃል፤

7) በዚህ መመሪያ መሰረት የምግብ ዘይትን የሚያስመጡ እና የሚያሰራጩ አካላትን ተደራሽ በሆነ መልኩ የግብይት ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

8) ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚጠቅሙ የክትትል፣ የድጋፍ እና ቁጥጥር ተግባራትን ያከናውናል፤

9) በዚህ መመሪያ መሰረት በማይፈጽሙ ላይ ማናቸውም አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ አስመጪዎች በሚሆኑበት ጊዜ ደግሞ ከአስመጪነት እንዲሰረዙ ወይም ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሙሉ መረጃዎችን በማቅረብ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመጨረሻ ውሳኔ ያስተላልፋል፤

10) የምግብ ዘይት ስርጭትን፣ ዋጋን እና ሌሎችም በመስኩ አስፈላጊ መረጃዎችን በየወሩ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀርባል፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ግብረመልስ በመቀበል እንዲተገበር ያደርጋል፤

11) በዘርፉ ሊሰማሩ የሚፈልጉ ድርጅቶችን ለመምረጥ የተጠቀሱ መስፈርቶችን በህዝብ ሚዲያ ያሳውቃል፤

12) የምግብ ዘይቶችን ለማስመጣት ለመሳተፍ ከሚመዘገቡ ድርጅቶች የሚቀርቡ ሰነዶችን በማጣራት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ድርጅቶችን በመምረጥ ሙሉ መረጃ በማያያዝ ለመጨረሻ ውሳኔ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ይልካል፤

Ministry Of Trade & Industry Archives
Ministry Of Trade & Industry Archives
መዝገብ ቤት

13) በማናቸውም ምክንያት ከአስመጪነት የሚሰረዙ ካሉ ክፍተት ሳይፈጠር በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል አማካኝነት ምትክ በመምረጥ በሚኒስቴሩ ማጸደቅ አለበት፤

14) ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ጠቃሚ የሆኑ ማናቸውንም ተግባራት ያከናውናል፤

15) ከሚንስቴር መስሪያ ቤቱ በሚተላለፈው የሥርጭት አፈጻጸም መመሪያ እና በሚመደበው ኮታ መሰረት ሸቀጦቹን እስከ ሸማቹ ህብረተሰብ ሲደርስ የሚያስችል የስርጭት አፈጻጸም፣ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዐት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙንም በሚዘረጋ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሳውቃል፤.

16) በክልሉ የሚሰራጭላቸውን ከተሞችና የአካባቢው መስተዳደሮች ማከማቻና ማሰራጫ ማዕከላትን ይለያል፣ በተገቢው ጊዜና መጠን ክምችት መያዙንና መሰራጨቱን ክትትል ያደርጋል፤

17) ለክልሉ የተደለደለውን የምግብ ዘይት በክልሉ ለሚገኙ ከተሞችና የአካባቢ መስተዳደሮች እንዲሁም የመንግስት ተቋማትን ይደለድላል ያሳውቃል፤

18) በአካባቢው መስተዳደሮች የተመረጡ ሸማች ማበራትና ቸርቻሪ ነጋዴዎችን ከተጠቃሚው ህብረተሰብ ጋር ትስስር ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤

19) በየጊዜው ስርጭቱ በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት፣ በተተመነው ዋጋ መሰረት መፈፀሙን ይከታተላል፣ ከተዘረጋው አሰራር ስርዓት ውጭ በሚያከማቹ፣ በሚያጓጉዙና በሚያከፋፍሉ ሸማች ህብረት ሥራ ማህበራት እና ቸርቻሪ ነጋዴዎች ላይ በየደረጃው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ህጋዊ እርምጃ ያስወስዳል፤ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የአፈፃፀም ሪፖርት በየወሩ ይልካል፤

20) የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚተምነውን የመሸጫ ዋጋ መነሻ በማድረግ እና እንደየርቀታቸው የትራንስፖርት ዋጋን መሰረት በማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ላልተመነባቸው በስሩ በሚገኙ ከተሞችና ለአካባቢው መስተዳደሮች የሚኖረውን የመሸጫ ዋጋ ይወስናል፣ ሥራ ላይም እንዲውል ያደርጋል፤

21) በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ከክልሉ የህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃ ኤጀንሲዎች ጋር በመሆን በሁሉም አካባቢዎች የምግብ ዘይቱን ለማከፋፈል የሚችሉ የህብረት ስራ ማህበራት ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያሳውቃሉ፤

22) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል።።

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

## 11. የምግብ ዘይት አስመጪ ግዴታ

1) የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያወጣው የዋጋ ግንባታ እና ትርፍ ህዳግ ብቻ የመሸጥ እና በወቅቱ የማስመጣትና ምርቱን ለተጠቃሚዎች በወቅቱ የማድረስ፤
2) ያስመጣውን መጠን፣ ዋጋ፣ ስርጭት እና ሌሎችም አስፈላጊ መረጃዎች በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን ለተሰጣቸው ወይም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት በየሳምንቱ አርብ እና ወር በገባ በ30ኛ ቀን የማስተላለፍ፤
3) በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል ጋር የዚህ መመሪያ አካል በሆነው አባሪ ቁጥር 1 መሰረት ውል የመግባት፤
4) የዚህ መመሪያ አካል በሆነው አባሪ ቁጥር 2 መሰረት በየወሩ ለተመረጡበት ክልል በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማሳወቅ፤
5) የምግብ ዘይት ግዢ በሚፈጽምበት ጊዜ ምርቱ የኢትዮጵያን አስገዳጅ ደረጃ ማሟላቱን ያስፈትሻል፣ ጥራት የሌላቸውን ምርቶች ለህብረተሰቡ ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደርጋል፣
6) በብሔራዊ የሥነ ምግብ ፕሮግራም ሐምሌ 2016 እና የምግብና ስርዐተ ምግብ ፖሊሲ ህዳር 2011 ሰነድ መሰረት የምግብ ዘይት ግዥ በማፈፀምበት ጊዜ ምርቱ በቫይታሚን A እና D የበለፀገ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡
7) አስመጪዎች በመካከላቸው ውድድር እንዲኖር ከአለም የመግዣ ዋጋና አማካኝ የፓኬጂንግ ዋጋ በታች በመቀነስ በሚስትር መ/ቤቱ ከሚተመነው የመሸጫ ዋጋ በታች መሸጥ ማቅረብ ይችላሉ፣ ሆኖም አስመጪዎች በሚንስትር መ/ቤቱ ከተቀመጠው የመሸጫ ዋጋ በላይ ያለመሸጥ፣
8) ተጠቃሚው ላይ የአቅርቦት መጉላላት ያለማድረስ እና ማቅረብ ያለበትን መጠን ሳያጓድል ማቅረብ፡፡

## 12. በዞን/በክፍለ ከተማ ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ተግባርና ኃላፊነት

1) የተመደበለትን ኮታ መጠን በሥሩ ለሚገኙ ወረዳዎች፣ ከተሞች፣ ለአገልግሎት ሰጪዎች እና መንግሥታዊ ተቋማት ይደለድላል፣ ያሳውቃል፣ ይከታተላል፤



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives
ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር Ministry Of Trade & Industry Archives መዝገብ ቤት

2) የወሩን የአቅርቦትና ስርጭት አፈጻጸም በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ሪፖርት ያቀርባል፤
3) የህብረት ስራ ማህበራት እና ቸርቻሪ ነጋዴዎችን በተወሰነለት ቁጥር መጠን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ይመርጣል፤
4) የህብረት ስራ ማህበራት እና የቸርቻሪ ነጋዴዎች የመግዣና የመሸጫ ዋጋ በተወሰነው መሰረት መፈፀሙን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤
5) በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል በተወሰነው መሰረት እንደቅደም ተከተላቸው በማከፋፈያ እና በችርቻሮ የመሸጫ ዋጋ መፈጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
6) ትስስር ለተፈጠረላቸው ቸርቻሪዎች እና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ምርቱን በአግባቡ ስለማሰራጨታቸው እና ለተገቢው ዓላማ ማዋላቸውን የሚገልፅ ማረጋገጫ ክሊራንስ/ደብዳቤ/ እያረጋገጠ በየወሩ ለአስመጪው ያሳውቃል፤
7) በወቅቱ ለየዞኑ/ክፍለ ከተማው የተመደበው ኮታ መድረሱን ያረጋግጣል፣ ችግር ካለም በክልሉ ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል በፅሁፍ ያሳዉቃል፣ መፍትሄም በፍጥነት እንዲሰጥ ያደርጋል፤
8) በታቀደውና በግልጽነት ለህብረተሰቡ መድረሱን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ከተቀመጠው አቅጣጫ ውጪ በሚንቀሳቀሱት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም ህጋዊ እርምጃም እንዲወሰድ ያደርጋል፤
9) በአጠቃላይ ስለስርጭቱ ከሚመለከታቸው መረጃዎችን በማሰባሰብ በቂ ትንተና ያደርጋል፣ የተከሰቱ ችግሮች ላይ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
10) በዚህ መመሪያ በሚሸፈኑ የምግብ ዘይት ስርጭት ቁጥጥርና ሌሎችም መሰል ተግባራት በተመለከተ አስፈላጊውን ያደርጋል፤

13. በወረዳ ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ተግባርና ኃላፊነት

1) የተመደበለትን ኮታ በወረዳው ለሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራትና ቸርቻሪ ነጋዴዎች ይመድባል፣ ለዞን/ክፍለ ከተማ ያሳውቃል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
2) በቂ ቁጥር ያላቸውን ቸርቻሪ ነጋዴዎችን /ማህበራቶች/ ለህብረተሰቡ ተደራሽነታቸው ከግምት በማስገባት ይመርጣል ያሰማራል፤

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

3) ቸርቻሪ ነጋዴዎችን፣ ህብረት ስራ ማህበራትንና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ከአስመጪ ድርጅቶች ጋር ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

4) በየወሩ የአቅርቦትና ስርጭት አፈጻጸም ሪፖርት ለዞኑ/ለክፍለ ከተማ ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ያደርጋል፣

5) በወረዳው የተመደበላቸው ኮታ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ተደራሽ መሆኑን በቅርብ ይከታተላል፣ ለሚከሰቱ ችግሮችም አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

6) ህብረተሰቡን በተደራጀ አኳኋን ከተመረጡ ቸርቻሪዎችና የህብረት ስራ ማህበራት ጋር አመቺ አደረጃጀቶች በመጠቀም ትስስር በመፍጠር አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

7) በተቀመጠው የዋጋ ተመን መሰረት ህብረት ስራ ማህበራት እና ቸርቻሮ ነጋዴዎች በተተመነው ዋጋ መሠረት ለተጠቃሚው እያሰራጩ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

14. የቸርቻሪዎች ግዴታ

1) ከአስመጪዎች የተረከቡትን የምግብ ዘይት ወቅቱን ጠብቀው በተቀመጠላቸው የትርፍ ህዳግ መሰረት ትስስር ለፈጠረላቸው ተጠቃሚዎች የማከፋፈል፤

2) የስርጭት/ሽያጭ እንቅስቃሴቸውን በተመለከተ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማቅረብ፤

3) ስለሽያጫቸዉ መረጃ የመያዝ፣ በተቆጣጣሪ አካላትም ሲጠየቁ የማቅረብ፤

4) ሌሎችም ለመስኩ ጠቃሚ የሆኑ ማንኛውንም ተግባራት የማከናወን፤

15.የቸርቻሪ የመመልመያ መስፈርት

1) በዘርፉ ለመሰማራት የሚያስችላቸው የፀና የችርቻሮ ንግድ ፈቃድ/የህብረት ስራ ማህበራት ምዝገባ እና የምግብ ዘይትን ለመቸርቸር አቅም ያለው፣

2) ባለፉት ዓመታት በንግድ ስራ እንቅስቃሴው መልካም ስነ ምግባር ያለው፣ በንግድ ወይም በታክስ ማጭበርበር ያልተቀጣ፣

3) ለአቅርቦትና ስርጭት በተዘረጋው ስርዓትና በሚወሰነው የዋጋ ተመንና የትርፍ ህዳግ መሰረት ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ፣

4) በዚህ መመሪያ መሠረት ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ፤



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

5) ንግድን በክልል ለማስተዳደር በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል መሰረት ሌሎች ተጨማሪ እና አስፈላጊ መመልመያ መስፈርቶች ሊጨምር ይችላል፡፡

## 16. ከምግብ ዘይት አስመጪነት ስለመሰረዝ

በዚህ መመሪያ እና የምግብ ዘይትን ለማስመጣት በገባው ውል መሰረት የማይፈጽም ሆኖ ሲገኝ ከአስመጪነት ሊሰረዝ ይችላል፡፡

## 17.የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርአት

1) ማንኛውም አስመጪ ድርጅት በመረጣ ሂደት አፈጻጸም ላይ ቅሬታ ካለው መረጣውን ላካሄደው በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን ለተሰጠው ኃላፊ ከመረጣው በኋላ በ5 ቀን ውስጥ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፤

2) ቅሬታ የቀረበለት በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው ሃላፊም ቅሬታውን አይቶ ቅሬታው ከቀረበለት በኋላ ባሉት 5 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት አለበት፤

3) ቅሬታ አቅራቢው በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠው ውሳኔን የማይቀበል ከሆነ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ውሳኔ ሳይሰጠው ከቀረ ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ ቀናቶች ውስጥ ወይም ለቅሬታው ምላሽ ካልተሰጠው ካመለከተበት ጊዜ ጀምሮ ከ5 ቀናት በኋላ ቅሬታውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፤

4) የሚኒስቴር መ/ቤቱ የቀረበለትን ቅሬታ ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ቀናት ውስጥ በማጣራት በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ውሳኔን በማጽደቅ ወይም በመሻር በጽሁፍ ለቅሬታ አቅራቢው ምላሽ መስጠት አለበት፤ የውሳኔውን ግልባጭ ለወሰነው አካል እንዲደርስና እንዲፈጸም ያደርጋል፣

5) የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

18. የዋጋ ትመናና የትርፍ ህዳግ ምጣኔ አወሳሰን፣

1) ሚንስቴር መ/ቤቱ የአለም ዋጋን መሰረት በማድረግ የአስመጪዎችና የቸርቻሪዎችን የመሸጫና የመግዣ ዋጋ ለተጠቃሚዎች በህዝብ ማስታወቂያ ያሳውቃል፡፡
2) ሚኒስትር መ/ቤቱ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዋጋን ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከአስመጪዎች ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት መረጃ ያሰባስባል አሰራሩንም በግልፅነት አሰራር ተመስርቶ በመስራት ያሳውቃል፣
3) አስመጪዎች የአለም የመግዣ ዋጋን መሰረት በማድረግ ይገዛሉ፣
4) ሸቀጡ የተገዛበት ሀገር የአምራች ድርጅት ስም እና ቼምበራይዝድ የሆኑ ኢንቮይሶች፣
5) ምርቱ የተጓጓዘበት የትራንስፖርት ድርጅት ዋጋ፣
6) ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

19. የትርፍ ህዳግ

1) በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱ የምግብ ዘይት አስመጪዎች ጅቡቲ የደረሰበት ዋጋ ላይ የ3 በመቶ የትርፍ መጠን እንዲያገኙ ይደረጋል፡
2) ቸርቻሪዎች የምግብ ዘይትን ከአስመጪዎች የገዙበትን ዋጋ 4 በመቶ ጨምረው ለተጠቃሚው መሸጥ አለባቸው፡፡

20. የመተባበር ግዴታ

1. በዚህ መመሪያ መሰረት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የምግብ ዘይትን በተመለከተ የሚታዩ ማናቸውንም አሉታዊ ጉዳዮች ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በወቅቱ ሪፖርት የማቅረብ፣ መረጃ የመስጠትና በማናቸውም መልኩ የመተባበር፤
2. የህግ አስከባሪ አካላት እና አስተዳደሮች በዚህ መመሪያ መሰረት በማይሰሩት ላይ አስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ እርምጃ በመውሰድ ሂደት የመተባበር፤

21. የተሻሩ መመሪያዎች እና አሰራሮች

"ከመሰረታዊ የንግድ ዕቃዎች መሐከል ስኳር፣ የምግብ ዘይት፣ ስንዴና የስንዴ ዱቄት ለህብረተሰቡ ለማሰራጨት ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር -002/2008 ዓ.ም" ውስጥ የምግብ ዘይትን የሚመለከቱት ሁሉም ድንጋጌዎች እና መመሪያ ቁጥር 16/2010 ተሽረዋል፤

Ministry Of Trade & Industry Archives

22. ስለ አባሪዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዘው የሚገኙ አባሪ ቁጥር I ፣II፣III የዚህ መመሪያ አካል ናቸው።

23. መመሪያዉን ስለማሻሻል

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

24. መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሀሴ ------------ ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

ፈትለወርቅ ገብረእግዚአብሔር አብርሃ
ሚኒስትር

ፈትለወርቅ ገ/እግዚአብሔር አብርሃ

ሚኒስትር



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

አባሪዎች

የምግብ ዘይት አስመጪዎች ውል ቅፅ 1

ቀን ---------------------------

<u>የምግብ ዘይት አስመጪዎች ውል</u>

ውል ሰጪ ፡- ሙሉ ስም --------------------------------------------

አድራሻ፡ ክልል ------------------------------ ዞን/ቀበሌ -------------------------------

ክፍለ ከተማ ------------------------------ ወረዳ /ቀበሌ---------------------------

ውል ተቀባይ ፤- ሙሉ ስም -----------------------------------

አድራሻ፡ ክልል ------------------------------ ዞን/ቀበሌ ------------------------------

ክፍለ ከተማ ------------------------------ ወረዳ /ቀበሌ---------------------------

የውል ሰጪ ግዴታ

የምግብ ዘይት አስመጪዎችን ለመምረጥ የወጣው መመሪያ ቁጥር 020/2011 መሰረት የመስራት ግዴታ አለበት

1. የውል ተቀባይ ግዴታ
   የምግብ ዘይት አስመጪዎችን ለመምረጥ የወጣው መመሪያ ቁጥር 020/2011 የተደነገጉ ድንጋጌዎች መሰረት የመስራት ግዴታ አለበት
2. እኔ ውል ሰጪ ---------------------------------- ከውል ተቀባይ ------------------------------ ጋር በገባነው ውል መሰረት የምግብ ዘይት ደረጃ ------------------------------ እና በቫይታሚን A እና D የበለፀገ (ES 6133-2018 ) መሰረት በ------------------------- ክልል ---------------- -----፤-------------------፤--------------------፤---------------------፤ዞኖች ወይም ------------------ ፤---------------፤-----------------፤ ወረዳዎች ምርቱ ሳይቆራረጥ ወቅቱን ጠብቆ በየጊዜው በመንግሥት በሚወሰነው የትርፍ ህዳግ ብቻ እና የተፈቀደውን -------------------- መጠን ሲያገድል የራሱን የሎጀስቲክና ሌሎች አገልግሎቶችን በመጠቀም በመረጣ ውድድሩ ላሸነፈበት በታዎች ለማቅረብ አምኜና ፈቅጄ ለውል ተቀባይ ውል የሰጠሁ ሲሆን ለዚህ ስራ እንዲያመች ለውል ተቀባይ -------------------፤-------------------፤------------------፤---------------------፤ እንዲሚላ የማመቻች መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡
3. እኔ ውል ተቀባይ ------------------- ከውል ሰጪ በወሰድኩት የምግብ ዘይት ደረጃው ---------- ---------------------- እና በቫይታሚን A እና D የበለፀገ ( ES 6133-2013 ) መሰረት

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

በ---------------------ክልል/ከተማ -----------------ዞን/ክፍለ ከተማ ----------------- ወረዳ/ቀበሌ------ ----------- የራሴ የሎጀስቲክና ሌሎችም አገልግሎቶችን ተጠቅሜ መጠኑን ወይም ጊዜውን ጠብቆ ያለምንም ምክንያት ለማቅረብ እና ለመምረጥ ያበቃኝን መመሪያ ቁጥር 020/2011 አምኜና ፈቅጄ የውል ግዴታ ውስጥ የገባሁ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

4. በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 173/ (1) ይህ ውል በተዋዋይ ወገኖች መሃል የፀና ሲሆን በፍትሀብሄር ህጉ ስለውል የተደነገጉ ድንጋጌዎች ለዚህ ውል አፈፃፀም የሚያገለግሉ መሆናቸውን ተስማምተናል።

## እማኞች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | አድራሻ | | | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል/ከተማ | ዞን/ክፍለ ከተማ | ወረዳ/ቀበሌ | |
| 1. | | | | | |
| 2. | | | | | |
| 3. | | | | | |

የውል ሰጪ

ሙሉ ስምና ፊርማ

-------------------------

የውል ተቀባይ

ሙሉ ስምና ፊርማ

-------------------------

ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

## የማሰራጫ ማዕከላት የየዕለት መከታተያ ቅፅ 2

| ተ.ቁ | ማዕከል | ባለ 25 ሊትር | | | ባለ 20 ሊትር | | | ባለ 10 ሊትር | | | ባለ 5 ሊትር | | | ባለ 3 ሊትር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መነሻ ክምችት | በዕለቱ የገባ | ቀሪ ክምችት | መነሻ ክምችት | በዕለቱ የገባ | ቀሪ ክምችት | መነሻ ክምችት | በዕለቱ የገባ | ቀሪ ክምችት | መነሻ ክምችት | በዕለቱ የገባ | ቀሪ ክምችት | መነሻ ክምችት | በዕለቱ የገባ | ቀሪ ክምችት |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት

የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅት ወርሃዊ ስርጭት መከታተያ ቅፅ 3

| ተ.ቁ | ማዕከል | መነሻ ክምችት | የተጓጓዘ መጠን | የተሸጠ መጠን | ቀሪ ክምችት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | ድምር | | | | |

1. በወሩ ምርቱን በመግዛት፣በማጓጓዝ እንዲሁም በማከፋፈል የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተለይተው ይቀርባሉ፡፡
2. የተወሰዱ እርምጃዎችና የተቀመጡ የመፍትሔ አስተያየት
3. ቀጣይ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ተለይተው ይቀረብ



ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Industry
Archives
መዝገብ ቤት